የሰበር መ/ቁ. 33513

ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

**ተጠሪ፡-** ዘውዴ ተናኘ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ክርክር በተጀመረበት በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/በአርሲ ዞን የጢዮ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ሥራውን ሽፍኜ እየሰራሁ ባለሁበት የሥራ መደብ ላይ ሊያሳድገኝ ይገባል በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የደረጃ እድገት ሊሰጥ ወይም ሊገኝ የሚችለው ሕግና ስርዓት መሰረት ተደርጐ በሚካሄደው ውድድር ነው፡፡ ከሳሽ ያቀረበው ጥያቄ ከዚህ ውጪ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ከሳሽ በጠየቀው የሥራ መደብ ላይ እድገት ይሰጠው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ በቀጥታ ያቀረበውን የደረጃ ዕድገት ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ የመወሰኑን



አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ ክስ የመሰረተው ከፍ ያለ ደመወዝ የሚከፈልበትን የሥራ መደብ ሸፍኜ ለሰራሁበት ጊዜ ተገቢው ክፍያ ይሰጠኝ በማለት ሳይሆን፣ በቦታው ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ የደረጃ እድገት ሊገኝ የሚችለው በሥራ ክርክር ችሎት ክስ በመመስረት ሳይሆን፣ በኮርፖሬሽኑ ፀንቶ ባለው የህብረት ስምምነት መሰረት ክፍት የሥራ መደብ መኖሩ ሲረጋገጥና ለሁሉም ሰራተኞች የውድድር ማስታወቂያ ወጥቶ ተወዳድሮ በማሸነፍ ነው በማለት አጥብቆ ተከራክሮአል፡፡ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደቻልነውም ተጠሪ በቀጥታ ክስ ከመመስረቱ ውጪ አመልካች በገለፀው አይነት ተወዳድሮ እድገቱን ያገኘ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክርም የረገርም ጊዜ አገልግሎቱ እና የትምህርት ማስረጃው ታይቶለት ዕድገቱ በፍ/ቤት ሊሰጠው እንደሚገባ ከመግለጽ አልፎ የተጨበጠ ነገር አላቀረበም፡፡ አንድ ሰራተኛ የደረጃ እድገት የሚያገኘው አመልካች ከገለፀው አሰራር ውጪ በሆነ ሁኔታ ነው ለማለትም አልቻለም፡፡ በእርግጥ ዕድገት በጠየቀበት ቦታ ላይ ተመድቦ ይሰራ የነበረው ሰራተኛ ባለመኖሩ የሱን ሥራ ሸፍኖ መስራቱንና የዕድገት ጥያቄውን ያቀረበውም ይህን መሠረት በማድረግ እንደሆነ በክርክሩ አመልክቶአል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ለተሠራ ተጨማሪ ሥራ ክፍያ መጠየቅ እና በአንድ የሥራ መደብ ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ ማለት በእጅጉ የተለያዩ ናቸው፡፡ አመልካችም በአቤቱታው እንደገለፀው ተጠሪ ተጨማሪ ሥራ ሸፍኖ ሰርቶ ከሆነ ስለምትክ ሠራተኞች አመዳደብ ኮርፖሬሽኑ ባለው መመሪያ ወይም አሠራር መሠረት ይገባኛል የሚለውን ክፍያ ከመጠየቅ አልፎ ከዕድገት አሰጣጥ ሕግና ሥርዓት ውጪ የደረጃ ዕድገት በፍ/ቤት እንዲሰጠው መጠየቁ አግባብ አይደለም ፡፡ በአሰሪና